# በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት እንዲሁም በተናጠል የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች የሚገዛ የአሰራር ሥርዓት ቃል ኪዳን

መጋቢት 2011

አዲስ አበባ

# <u>በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት እንዲሁም በተናጠል የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች የሚገዛ የአሰራር ሥርዓት ቃል ኪዳን</u>

## <u>መግቢያ</u>

በአገራችን ጠንካራ እና ዘላቂ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት የተጀመረው የሪፎርም ስራን በጋራ ማሳካት እና ችግሮችን ከምንጮቻቸው የሚያደርቁ በረጅም ጊዜ እይታ የተቃኙ እርምጃዎችን መውሰድ በሀገር እና በህዝብ ላይ ሲፈፀም የኖረውን ውስብስብ የአስተዳደር በደል፣ ስር የሰደደ ኢ-ፍትሃዊ አሰራር እና ኢ-ዲሞክራሲያዊ አካሄድ መሰረታዊ በሆነ መልኩ በመቀየር እንደ አገር በፊታችን የተደቀነውን አስከፊ ሁኔታ የህልውና አደጋ ለማስወገድ ብቸኛው አማራጭ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፤

ከነባራዊው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ሁኔታዎቻችን በመነሳት እና ለህዝብ ፍላጎት በመገዛት ከላይ የተጠቀሰውን ሰፊ የሪፎርም ስራ ከግብ ለማድረስ በቅድሚያ በመላው ኢትዮጵያ ሰላም እና መረጋጋት እንዲሁም የህግ የበላይነት መረጋገጥ ያለበት መሆኑን በመገንዘብ፤

ይህን ለማድረግም ሁሉም ዜጋ እና የማህበረሰብ ክፍል በተረጋጋ ሁኔታ፣ በንቃት እና በስፋት መሳተፉ ፍፁም አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ዘላቂ ዋስትና ያለው ዲሞክራሲ እንዲሰፍን፣ ኢኮኖሚዊ እና ማህበራዊ እድገት እንዲፋጠን፣ በሕግ የበላይነት እና በህዝቡ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ በጋራ ለመገንባት አብሮ መሥራት የሚገባ በመሆኑ፤

እንዲሁም በአገራችን እየተፈጠረ ያለውን የዲሞክራሲ መድረክ ለህዝቦች አብሮነት፣ መቻቻል፣ መተሳሰብ እና ሕገ-መንግስታዊ መብቶች መከበር ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ለማስቻል በሚደረገው ሀገራዊ ንቅናቄ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሚኖራቸው ሚና ልዩ እውቅና በመስጠት ከፍተኛ ትኩረት ስላገኘ፤

የተለያዩ ሀሳቦችን እና የማህበረሰብ ድምፆችን የሚወክሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዲሞክራሲ ግንባታ፣ የሕግ የበላይነት መስፈን እና በሰላም መረጋገጥ ከመንግሥት ያላነሰ አይተኬ ሚና እና ሃላፊነት ያላቸው መሆኑን በመገንዘብ፤

በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚስተዋለው አሳሳቢ የሰላም መደፍረስ የተጀመረውን ሰፊ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ንቅናቄ ወደ ኋላ እንዳይመልሰው የፖለቲካ ፓርቲዎች ተቋማዊ እና ቀጣይነት ባለው የአደረጃጀት መድረክ አማካይነት እየተወያዩ የመፍትሄው አካል እንዲሆኑ ማስቻል ፍጹም አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት፤

የፖለቲካ ፓርቲዎች ኃላፊነት በተሞላበት አካሄድ የአገርን ብሔራዊ ደህንነት የዜጎችን ነፃነት እና መሰረታዊ መብት በዘላቂነት ማስጠበቅ በሚያስችል ደረጃ መሳተፋቸውም ተገቢ ስለሆነ፤

በሀገራችን በቀጣይ የሚደረገውን ብሔራዊ እና የአካባቢ ምርጫ ነፃ፣ ፍትሃዊ እና ዲሞክራሲያዊ ለማድረግ ሰላም እና መረጋጋት እንዲሰፍን የሁሉንም አስተዋጽኦ እና ትኩረት የሚጠይቅ በመሆኑ፤

ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ደጋፊዎቻቸው የዜጎችን እና የሌሎችን የፖለቲካ ድርጅቶች አባላት እና ደጋፊዎች ሕገ-መንግሥታዊ መብት እና ግዴታዎችን ባከበረ መልኩ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ለማድረግ ይቻል ዘንድ፤

እኛ በኢትዮጵያ ውስጥ የምንገኝ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዛሬ በነፃ ፈቃዳችን ይህን የፖለቲካ ፓርቲዎች የአሰራር ሥርዓት የጋራ ቃል ኪዳን በመመስረት ሰነዱ ለሀገራችን ሕዝቦች እና መንግሥት በይፋ እንዲገለጽ በፊርማችን አጽድቀናል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ የአሰራር ሥርዓት ሰነድ "**በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት እንዲሁም በተናጠል የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች የሚገዛ የአሰራር ሥርዓት ቃል ኪዳን**"፤ ከዚህ በኋላ "**የቃል ኪዳን ሰነድ**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ ውስጥ፤

2.1 "ሕገ-መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ነው፡፡

2.2 "የፖለቲካ ፓርቲ" ማለት በአገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ በመሳተፍ፤ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ በምርጫ አዋጁ ድንጋጌ መሰረት በፖለቲካ ፓርቲነት ወይም በፓርቲዎች ግንባር ወይም ቅንጅት የተመዘገበ፤ ወይም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአዋጁ መሰረት በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለመመዝገብ በሂደት ላይ ያለ ድርጅት ነው፡፡

2.3 "የጋራ ምክር ቤት" ማለት በዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ አንቀጽ 15 መሠረት በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ፈቃድ የሚመሰረት የጋራ ምክር ቤት ነው፡፡

2.4 "የፖለቲካ ፓርቲ አመራር" ማለት በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ፓርቲውን በመወከል እና በውሳኔ ሰጭነት የሚሳተፍ ማለት ነው፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የቃል ኪዳን ሰነድ፤

3.1 የቃል ኪዳን ሰነዱን ተስማምተው በፈረሙ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ እና

3.2 በፖለቲካ ፓርቲዎቹ አመራር፣ አባላት፣ ወኪሎች እና ተጠሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማ

ይህ የቃል ኪዳን ሰነድ የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

4.1 የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ አመራሮቻቸው እና አባሎቻቸው የሚያደርጉትን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ በማገዝ በሀገራችን የተጀመረውን የዲሞክራሲ ግንባታ ማጠናከር እና ዘላቂ እንዲሆን ማስቻል፤

4.2 በፓርቲዎች መኃል ሊነሳ የሚችለውን አለመግባባት በጋራ መፍታት፤

4.3 በሀገራችን የሕግ የበላይነትን በማስፈን ሰላም እና መረጋጋት እንዲኖር ለማስቻል፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና አባሎቻቸው በኃላፊነት እንዲንቀሳቀሱ እና በዚህ ረገድ ከዚህ ጋር በተያያዘ መንግሥት የሚያደርገውን ጥረት እንዲደግፉ ለማድረግ የሚያስችል የጋራ መድረክ መፍጠር እና ስልት መንደፍ፤

4.4 የዜጎች ሕገ-መንግሥታዊ መብት ሳይሸራረፍ እንዲከበር እና እንዲረጋገጥ የሚያስችል አሰራር እና የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዲኖር ማገዝ፤

4.5 መጪው ብሔራዊ እና አካባቢያዊ ምርጫ ነፃ እና ፍትሃዊ እንዲሆን በሚደረገው ዝግጅት የፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸውን ተሳትፎ እና ሚና ማጎልበት፤ እና

4.6 ጠንካራ የመድብል ፓርቲ ሥርዓት ለመመስረት የሚደረገውን ጥረት ማገዝ ናቸው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>መሰረታዊ ድንጋጌዎች</u>

### 5. <u>ሕገመንግሥታዊነት</u>

5.1 ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች የሕገ-መንግሥቱን የበላይነት የመቀበል እና ህገመንግሥቱን የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡

5.2 ይህ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግዴታ በዋናነት ማናቸውም ሕገ-መንግሥቱን የሚፃረሩ ድርጊቶችን አለመፈፀምን እና እንዲፈፀሙ አለማድረግን ይጨምራል፡፡

5.3 የሥልጣን ገደብን፣ በሕግ ፊት እኩል መሆንን፣ የሕግ አተገባበር ሥነ-ሥርዓት መጠበቅን፣ የሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበርን መሠረት ያደረገ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲመሰረት እና እንዲረጋገጥ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በሙሉ ሀገራዊ ስሜት እና ኃላፊነት ይንቀሳቀሳሉ፡

5.4 ከላይ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የፖለቲካ ፓርቲዎች ህጋዊ እና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሕገ-መንግሥቱ እንዲሻሻል የመጠየቅ፣ ይዘቱን የመተቸት ወይም ሙሉ በሙሉ እንዲቀየር ለማድረግ ሕዝብን የማሳመን ስራ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

## 6. <u>የሕግ የበላይነት እንዲከበር የማድረግ ግዴታ</u>

6.1 ማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የፓርቲ አመራር፣ አባል ወይም ደጋፊ ከሕግ በላይ አይደለም፡፡ በመሆኑም በሕገ-መንግሥቱ የተቀመጡ የግል እና የቡድን መብቶች እና ነፃነቶች እንዳይገፈፉ፣ እንዳይሸራረፉ ወይም እንዳይጣበቡ፣ እንዲሁም በሕገ-መንግሥቱ የተመለከቱ የስልጣን ገደቦች እና የመንግሥት አሰራር ሥርዓቶች እንዳይጣሱ ለማድረግ ተገቢውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል፤ አግባብነት ያላቸው እርምጃዎችንም ይወስዳል፡፡

6.2 ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በማናቸውም መልኩ ከሚገለፁ የኃይል አሰራሮች፣ ከሁከት እና ከአመፃ ድርጊቶች የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

6.3 የፖለቲካ ፓርቲዎች አጀንዳዎቻቸውን በፀኑ ህጎች ብቻ እየተመሩ የማከናወን እና በማናቸውም እንቅስቃሴዎቻቸው ሕግ እና ሥርዓትን የመከተል ኃላፊነት እንዳለባቸው ይገነዘባሉ፡፡ ልዩነትም ሆነ ቅሬታ ሲኖራቸው በዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ የተቀመጡ ሥርዓቶችን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎችን በመከተል መብቶቻቸውን እና ጥቀሞቻቸውን ያስጠብቃሉ፡፡

6.4 የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉንም አባላት እና ተከታዮቻቸውን ስለ የሕግ የበላይነት የማስተማር፣ እንዲሁም የዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ ይዘት በአባላት እና ደጋፊዎቻቸው እንዲታወቅ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 7. <u>ኃይል የመጠቀም ሥልጣን የመንግሥት ብቻ ስለመሆኑ</u>

7.1 ኃይልን የመጠቀም ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣን (monopoly of coercive power) የመንግሥት ብቻ ነው፡፡ ለዚህም መርህ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ተገዢ ይሆናሉ፡፡ በመንግሥት የአሰራር ሂደትም ያልተመጣጠነ የሀይል አጠቃቀም

እንዳይኖር አግባብነት ያላቸው የህገመንግሥት መርሆዎች እና የአለም አቀፍ ህግ ድንጋጌዎች እንዳይጣሱ በጋራ ይሰራሉ፡፡

7.2 ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አመራር፣ አባል ወይም ደጋፊ በምንም ሁኔታ ሕግን በማስፈጸም ተግባር ውስጥ በመግባት ለራሱ ወይንም ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚኖረው ግንኙነት የራሱን ጥቅም በፍትህ ስም ማስፈፀም እንደማይችል ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ግንዛቤ ይወስዳሉ፡፡

7.3 መንግሥት የሕግ የበላይነት መርህን መሰረት በማድረግ የዜጎችን እና የተቋማትን የአካል፣ የሕይወት እና የንብረት ደህንነት ከተራ የወንጀል ድርጊት (conventional crime) ከፖለቲካዊ ረብሻዎች (political unrest/violence) እና ከግለሰቦች አመፃ (violence pursued as vigilante justice) የመጠበቅ እና ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚነሱ የደህንነት እና የፀጥታ ስጋቶችን የመከላከል ኃላፊነት አለበት፡፡ ለዚህ መርህ ተግባራዊነትም ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሙሉ ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

7.4 የፖለቲካ ፓርቲዎች ከሥርዓት አልበኝነት እና አመፃ የፀዳ ሥርዓት እና ማህበረሰባዊ እሴት ለመፍጠር በየፊናቸው ተጫባጭ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡ በአባላት እና ተከታዮቻቸውም ዘንድ እነዚህ እሴቶች እንዲታወቁ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 8. <u>የፖለቲካ ፓርቲዎች በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል እንቅስቃሴ የማድረግ ሕገመንግሥታዊ መብት</u>

8.1 የእጩ አቀራረብን በተመለከተ ስለክልላዊና አገራዊ ፓርቲዎች በህግ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተለያየ አመለካከትን የሚወክሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብሔራዊ ስብጥራቸው፣ የሚመሩበት ፕሮግራም ወይም የሚያራምዱት ርዕዮተ-ዓለም ምንም ይሁን ምን በማናቸውም ጊዜ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል የመንቀሳቀስ፣ የፖለቲካ ዓላማቸውን፣ ሀሳባቸውን እና መርሆቻቸውን የማስተዋወቅ፣ አባላትን የመመልመል፣ ጽ/ቤት የመክፈት፣ ምርጫ-ነክ ሥራዎችን የማከናወን እና ሌሎች ሕጋዊ የፓርቲ ሥርዎቻቸውን የማካሄድ ሙሉ ነፃነት አላቸው፡፡

8.2 የሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በየትኛውም ጉዳይ ላይ ሊኖር የሚችል የዓላማ፣ የሃሳብ ወይም የዘር ልዩነትን፣ ወይም ሌላ ምክንያት መሰረት በማድረግ የሌሎች ፓርቲዎችን መብቶች የሚፃረሩ ወይም የሚያጣብቡ ድርጊቶችን ከመፈፀም የመቆጠብ ግዴታ አለባቸው፡፡

8.3 ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የራሱ አባላት ወይም ደጋፊዎች በሚበዙበት አካባቢ ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ በነፃነት እንዳይንቀሳቀስ የሚያግዱ ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ ለአባላት እና ደጋፊዎቹ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ይሠራል፤ አስፈላጊ የመከላከል እርምጃዎችን ሁሉ ይወስዳል፤ ድርጊቶቹ ተፈጽመው ሲገኙም ለማስቆም እና አጥፊዎችን ሕግ ፊት ለማቅረብ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

8.4 ከላይ የተዘረዘሩት አሠራሮች በየትኛውም ደረጃ ያሉ የመንግሥት አካላት እንዲያስከብሩ ፓርቲዎች በጋራ ይሰራሉ፡፡

## 9. <u>በፖለቲካ እንቅስቃሴ ሂደት የሌሎች አካላትን መብት ስለማክበር</u>

9.1 የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ የሕዝብን ወይም የማናቸውንም ማህበረሰብ ክፍልን መሰረታዊ መብት እና ነፃነት በሚጥስ ወይም በሚገድብ መልኩ ሊፈፀም እንደማይችል እና እንደማይገባ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስምምነት አድርገዋል፡፡

9.2 ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እንቅስቃሴውን የሚያካሂደው የራሱንም ሆነ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎችን አባላት ወይም ደጋፊዎች፣ እንዲሁም በየትኛውም አካባቢ የሚገኝ የሕብረተሰብ ክፍል ወይም ሕዝብ መብት እና ነፃነትን በሚያከብር አግባብ ብቻ ይሆናል፡፡

## 10. <u>የስብሰባዎች ሕዝባዊ ሰልፎች እና ሌሎች ሁኔታዎች አፈፃፀም</u>

10.1 ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የሚያካሂዳቸው የድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ሰልፎች ስብሰባዎች እና ተመሳሳይ ዝግጅቶች የፓርቲውን ሕጋዊ ዓላማ እና ተግባራት

ለማስፈጸም እና በሕግ የተጠበቁ መብቶቹን ለመተግበር ብቻ የሚከናወኑ ሕጋዊ ሁነቶች መሆን አለባቸው፡፡

10.2 ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ዓላማዎቹን ለማሳካት ከሚያስፈልጉ ሕጋዊ ተግባራት ውጭ ያሉ የሌሎች አካላትን መብቶች ሊጥሱ ወይም ሌሎችን ለጠብ ሊያነሳሱ የሚችሉ በዘር፣ በብሔረሰብ፣ በብሔር፣ በጎሣ፣ በሃይማኖት ወይም በሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተመሠረቱ ድርጊቶችን ከመፈፀም የመቆጠብ ግዴታ አለበት፣ መሰል ድርጊቶች በአባላት ወይም ደጋፊዎች እንዳይፈጸሙም ተጨባጭ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

10.3 ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በየዝግጅቶቹ ሊተላለፉ የተፈለጉ መልዕክቶችን ሥርዓት ባለው መልኩ ከማካሄድ ውጪ ማንኛውንም የሕብረተሰብ ክፍል በአሉታዊ መልኩ ሊስሉ ወይም ሊገልጹ የሚችሉ ድርጊቶችን መፈጸም የለበትም፤ በአባላቱ ወይም ደጋፊዎቹ እንዳይፈፀሙ የማድረግ ግዴታም አለበት፡፡

10.4 ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዝግጅቶቹ የሚሳተፉ ሰዎች ማናቸውንም ዓይነት ባህላዊ ወይም ዘመናዊ የጦር መሣሪያ፣ ስለት፣ ተቀጣጣይ ነገር፣ ወይም ሌላ ሰው ሊጎዳ የሚችል ቁስ እንዳይዙ ያስገነዝባል፣ ይከላከላል፡፡ ይህ አሠራር እንደየአካባቢው ባህል የሚያዙ መሳሪያዎችን አይመለከትም፡፡

10.5 ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ለዝግጅቶች የተጠቀመባቸውን አርማ፣ የጽሑፍ መልዕክት እና ሌሎች ቁሳቁሶችን ዝግጅቱ በተከናወነ በ24 ሰዓት ውስጥ ማንሳት አለበት፡፡

10.6 ለቁጥጥር፣ ለደህንነት እና ለጥበቃ እንዲያመች በማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ ሊካሄድ የታሰቡ ዝግጅቶች ጊዜ እና ቦታ ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ ካዘጋጃቸው ወይም ሊያዘጋጃቸው ከሚችሉ ሁኔታዎች ጋር እንዳይደራረቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች እርስ በርስ እና ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት ጋር መረጃ ይለዋወጣሉ፡፡

## 11. ስለሚዲያ እና ማህበራዊ ገፆች አጠቃቀም እና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት

11.1 የመንግሥት እና የግል ሚዲያዎች በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ዴሞክራሲያዊ ባህልን ለማሳደግ በሚችሉበት መልኩ እንዲቃኙ ለማድረግ እና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እና ማሕበረሰብ ግንባታ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ለማስቻል የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ስልቶች እና መርሃ-ግብሮችን ያወጣሉ፡፡ ሆኖም የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚዲያ ተቋማቱን አሰራሮች እና ነፃነት ከሚጋፉ ማናቸውም ሥራዎች መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡

11.2 በፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆነ በደጋፊዎቻቸው ባለቤትነት የሚተዳደሩ የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች፣ ድረ ገጾች የፓርቲ ልሳንን ጨምሮ የህትመት ውጤቶች፣ የቴሌቪዥን እና የሬዲዮ ጣቢያዎች፣ በተመሳሳይ እሴቶች እንዲቃኙ፣ እንዲሁም ማሕበረሰባዊ ጥላቻን፣ መቃቃርን፣ አመፃን፣ መለያየትን እና ሕገወጥ ድርጊቶችን የሚያደፋፈር ውጤት ያላቸው መልዕክቶችን ከማስተናገድ እንዲቆጠቡ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

11.3 የፖለቲካ ፓርቲዎች ራሳቸው በባለቤትነት ወይም በበላይነት የሚያስተዳድሯቸውን የማሕበራዊ ግንኙነት ገፆች፣ ሌሎች ድረ-ገጾች እና ሚዲያዎች ዝርዝር ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## 12. የፖለቲካ ፓርቲዎች ተጠያቂነት እና እርምጃ የመውሰድ ግዴታ

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በአመራሩ ወይም በአባላቱ በሚፈፀሙ ይህን የቃል ኪዳን ሰነድ ወይም ሌላ አግባብነት ያለውን ሕግ በጣሱ ድርጊቶች ምክንያት ለሚፈጠር ጉዳት ኃላፊነት ይወስዳል፤ ድርጊቶቹን በይፋ ያወግዛል፤ የደረሰውን ጉዳት ለመካስ ወይም ለመጠገን የሚያስችሉ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤ የድርጊቱን ፈፃሚዎች በሕግ አግባብ እንዲጠየቁም መረጃ እና ማስረጃዎችን መስጠት ጨምሮ ማንኛውንም ትብብር ያደርጋል፡፡

## 13. የመንግሥት ሃብት እና ሥልጣን ለፖለቲካ ሥራ አለመጠቀም

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የፖለቲካ ፓርቲ አመራር፣ አባል፣ ወይም ተጠሪ፡-

13.1 ማንኛውንም የመንግሥት ሃብት (ገንዘብ፣ የሰው ሀይል፣ ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ንብረት፣ አላቂ ዕቃ ወዘተ) እና ሥልጣን ለፖለቲካ ፓርቲ ሥራ ጥቅም ላይ አያውልም፡፡

13.2 የመንግሥት መዋቅርን እና የሰው ሀብት በመጠቀም የገቢ ማሰባሰቢያ እንቅስቃሴ ማድረግ የለበትም፡፡

13.3 ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ያለውን የመንግሥት ሥልጣን በመጠቀም የመንግሥት፣ የግል እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ንብረቶች በማስገደድ ወይም ተፅእኖ በመፍጠር መጠቀም አይችልም፡፡

## ክፍል ሦስት

## የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ም/ቤት

14.1 በዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ ተ.ቁ 15 ላይ የሰፈሩትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ እንዲሁም በቃል ኪዳኑ ሰነድ ተራ ቁጥር 16 ላይ የተገለፁትን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የዚህ ሰነድ ፈራሚ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ም/ቤት ያቋቁማሉ፡፡

14.2 እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ አንድ አንድ ሰው በመመደብ በእኩል ቁጥር በጋራ ም/ቤቱ ይወከላል፡፡

14.3 እያንዳንዱ የም/ቤቱ አባል እኩል የሆነ ድምፅ አለው፡፡

14.4 የጋራ ም/ቤቱ በየ6 ወሩ ሰብሳቢውን፣ ም/ሰብሳቢውን እና ጸሐፊውን ይመርጣል፡፡ የስራ ዘመናቸውን እንዲሁም ዝርዝር ተግባር እና ኃላፊነታቸው የጋራ ምክር ቤቱ በሚያወጣው የውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡

14.5 የጋራ ም/ቤቱ በዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ ላይ የሰፈረውን ዓላማ እንዲሁም ተግባርና ኃላፊነት ዳር የሚያደርሰው የም/ቤቱ አባላትን በተለያዩ ኮሚቴዎች ለተለያዩ ሥራዎች እንደ አስፈላጊነቱ በመመደብ ይሆናል፡፡ ዝርዝሩም ም/ቤቱ በሚያወጣው የውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡

14.6 የጋራ ም/ቤቱ ሥራውን የሚያከናውነው የምርጫ ቦርድ በሚሰጠው ቢሮ ውስጥ ይሆናል፡፡

14.7 የጋራ ም/ቤቱ ለሥራው መሳካት አስፈላጊ ነው ብሎ ባመነ በማናቸውም ጊዜ ቦርዱ ሰራተኛ ወይም ኤክስፐርት በቋሚነትና በጊዜያዊነት እንዲመድብለት መጠየቅ ይችላል፡፡ ቦርዱም የተጠየቀውን ሰራተኛ ወይም ኤክስፐርት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ይመድባል፡፡

14.8 ም/ቤቱ ያቋቋማቸው ኮሚቴዎች በሰጡት ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ለጋራ ም/ቤቱ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ በሚቀርበውም ቅሬታ ላይ የጋራ ም/ቤቱ መርምሮ በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

14.9 የጋራ ም/ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በዓመቱ ውስጥ 4 ጊዜ ያህል ይኖረዋል፡፡

14.10 የጋራ ም/ቤቱን ከመደበኛ የስብሰባው ጊዜ ውጭ መጥራት የሚያስፈልግ ጉዳይ ሲኖር የጋራ ም/ቤቱ 1/3 አባላት ወይም የምርጫ ቦርድ መጥራት ይችላሉ፡፡

14.11 የጋራ ም/ቤቱ ምልዓተ ጉባኤ ተሟልቷል የሚባለው የም/ቤቱ 50+1 አባላት በተጠራው ስብሰባ ላይ ሲገኙ ነው፡፡ ይሁንና በመጀመሪያው ስብሰባ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ ሌላ ስብሰባ እንዲጠራ ይደረጋል፡፡ በዚህ ሁለተኛ የስብሰባ ጥሪ በተገኙት አባላት ስብሰባውን ያካሂዳል፡፡

14.12 ሰብሳቢው የም/ቤቱ ጉባኤዎች ይመራል፡፡ ም/ሰብሳቢው ሰብሳቢው በሌለበት ጊዜ ተክተው ይሰራሉ፡፡

14.13 የጋራ ም/ቤቱ ዓላማውንና ተግባርና ኃላፊነቱ ለመወጣት የሚያስችለው እንዲሁም አሰራሩን የሚመራበት የውስጥ ደንብ ያወጣል፡፡

## 15. <u>የጋራ ምክር ቤቱ ዓላማ</u>

15.1 በሀገራችን የተጀመረውን የዲሞክራሲ ግንባታ ሪፎርም ለማጠናከር እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለባቸውን ህጋዊ ኃላፊነት በዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ መሰረት ለማስፈፀም ተቋማዊ አካል ሆኖ ማገልገል፤ እና

15.2 በፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም በፖለቲካ ፓርቲዎች እና በመንግሥት መካከል አለመግባባቶች ሲከሰቱ በውይይት እና በመግባባት ለመፍታት የሚያስችል የውይይት እና የምክክር አካል ሆኖ ማገልገል፤ እንዲሁም በፈራሚዎች መሀል የተፈጠሩ ግጭቶችን በዚህ ሰነድ አግባብ ውሳኔ መስጠት ናቸው፡፡

## 16. <u>የጋራ ምክር ቤቱ ተግባር እና ኃላፊነት</u>

16.1 ለዜጎች ሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ፓርቲዎች የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

16.2 በፓርቲዎች መካከል በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በሚነሱ አለመግባባቶች እና ጥያቄዎች ላይ በመወያየት ችግሮችን የሚፈታ መድረክ ሆኖ ያገለግላል፤

16.3 የቃል ኪዳን ሰነዱን ይዘት አስመልክቶ ፓርቲዎች ለአባሎቻቸው እና ለደጋፊዎቻቸው ትምህርት መስጠታቸውን ያረጋግጣል፤

16.4 ይህ የቃል ኪዳን ሰነድ በሁሉም ፈራሚዎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ተፈጻሚ መሆኑን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

16.5 የዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ ይዘት ተጥሷል የሚል ቅሬታ ሲቀርብለት ከቅሬታው ጋር በቀጥታ ግንኙነት ከሌላቸው ፓርቲዎች የተውጣጣ አጣሪ ኮሚቴ በማቋቋም ጉዳዩን ያጣራል፤ ይመረምራል፤

16.6 ተጣርቶ በተገኘው ውጤት ላይ በመመስረት አስፈላጊውን የመፍትሔ አቅጣጫ ቀይሶ በፓርቲዎች የተባበረ ጥረት እንዲተገበር ያደርጋል፤

16.7 በዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ የተገለፁ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚተላለፉ የጋራ ውሳኔዎች እንደ አስፈላጊነቱ በመገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

## 17. <u>አቤቱታዎች ወይም አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት ሁኔታ</u>

17.1 አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተቀመጡ መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ ይዘት ተጥሷል ብሎ የሚያምን ወገን በማስረጃ የተደገፈ አቤቱታውን ለጋራ ምክር ቤቱ ማቅረብ ይችላል፡፡

17.2 ለጋራ ምክር ቤቱ የሚቀርቡ አቤቱታዎች አቀራረብ፣ የማስረጃ አሰባሰብ፣ አቤቱታን መሰረት ያደረጉ ምርመራዎች እንዲሁም ውሳኔዎች የሚሰጡበትን ሥርዓት የሚመራው ምክር ቤቱ በሚያወጣው የውስጥ ደንብ ይሆናል፡፡

17.3 የጋራ ምክር ቤቱ በቀረበለት ማናቸውም ውሣኔ በሚያስፈልገው ጉዳይ ላይ በቂ የሆነ ውይይት ካደረገ በኋላ በስምምነት (consensus) ውሣኔ ለመስጠት ተገቢውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

17.4 ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 17.3 በተገለፀው ሁኔታ በስምምነት (consensus) ውሳኔ ማስተላለፍ ሳይቻል ሲቀር ውሳኔው በተገኙ አባላት 3/4ኛ ድምጽ በቀረበው ጉዳይ ላይ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

## 18. <u>የቃል ኪዳን ሰነዱ ይዘት ጥሰቶች እና ስለሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፤ የፖለቲካ ፓርቲ አመራር፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ፣

18.1 በዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ ውስጥ የተካተቱትን ግዴታዎች ያልተወጣ እንደሆነ፣ በዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ የተከለከሉ ድርጊቶችን የፈጸመ እንደሆነ ወይም ዓላማውን በሚፃረር መልኩ ከተንቀሳቀሰ ይህን ቃል ኪዳን እንደጣሰ ይቆጠራል፡፡

18.2 ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ የፖለቲካ ፓርቲ ስህተቱን እንዲያርም፣ እንዲያስተካክል ወይም አግባብነት ያለውን እርምጃ እንዲወስድ የጋራ ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡

18.3 የጋራ ምክር ቤቱ እንደ አስፈላጊነቱ የቃል ኪዳን ሰነዱን የጣሰውን የፖለቲካ ፓርቲ ስም እና ተግባር ጠቅሶ ለሕዝብ እንዲጋለጥ ያደርጋል፤ ውሳኔውንም በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ሕዝቡ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

18.4 የጋራ ምክር ቤቱን ተደጋጋሚ ግሳጼ እና ማስጠንቀቂያ ለማድመጥ እና ከተነቀፈ ድርጊቱ ለመታቀብ ባልፈለገ ወይም ባልጣረ ድርጅት ላይ የጋራ ምክር ቤቱ ከምክር ቤቱ እስከማስወጣት የሚደርስ እርምጃ ለመውሰድ ይችላል፡፡

18.5 በዚህ ሰነድ ላይ የተደነገጉትን ሁኔታዎች ጥሷል ተብሎ ውሳኔ የተሰጠበት የፖለቲካ ፓርቲ ውሳኔው የተፈፀመ ስለመሆኑ ምክር ቤቱ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፡፡

## 19. ማሻሻያ

ይህ የቃል ኪዳን ሰነድ ከፈረሙት የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ቢያንስ ሩብ (1/4ኛ) የሚሆኑት የማሻሻያ ጥያቄ ሲያቀርቡ በቀረበው የማሻሻያ ጭብጥ ላይ ምክር ቤቱ በስምምነት (consensus) ውሣኔ መስጠት ካልቻለ በምክር ቤቱ በተገኙ አባላት 3/4ኛ ድምፅ የማሻሻያ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

## 20. የሚጸናበት ጊዜ

ይህ የቃል ኪዳን ሰነድ፤ ስማቸው ከዚህ በታች የተመለከተው የፖለቲካ ፓርቲዎች በሰነዱ ለመገዛት ተስማምተው ፊርማቸውን በሰነዱ ላይ ካኖሩበት ከዛሬ መጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት | | |
| 2 | የኢትዮጵያ ሰላማዊ የዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 3 | የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር | | |
| 4 | የኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 5 | የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት | | |
| 6 | ገዳ ሥርዓት አራማጅ ፓርቲ | | |
| 7 | የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት | | |
| 8 | መላው ኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 9 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ | | |
| 10 | የመላው ኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ንቅናቄ | | |
| 11 | ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 12 | የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ | | |
| 13 | የወለኔ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 14 | የመላው ኦሮሞ ህዝብ ዲሞክራቲክ ፓርቲ | | |
| 15 | የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ | | |
| 16 | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ | | |
| 17 | ሰማያዊ ፓርቲ | | |
| 18 | የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ | | |
| 19 | አዲስ ትውልድ ፓርቲ | | |
| 20 | የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ | | |
| 21 | አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ | | |
| 22 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ኮንግረስ | | |
| 23 | ምክክር ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ | | |
| 24 | የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ | | |
| 25 | ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ | | |
| 26 | የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 27 | ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 28 | የምዕራብ ሶማሌ ዲሞክራቲክ ፓርቲ | | |
| 29 | የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ | | |
| 30 | የኦሮሞ አቦ ነጻነት ግንባር | | |
| 31 | የደንጣ፣ ዱባሞ ክችንችላ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 32 | የከምባታ ሕዝቦች ኮንግረስ | | |
| 33 | የትግሪ ወርጂ ብሔረሰብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 34 | የኦሮሞ ነጻነት አንድነት ግንባር | | |
| 35 | የዶንጋ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 36 | የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ | | |
| 37 | የኢትዮጵያዊያን አንድነት ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 38 | የኢትዮጵያ ሶማሌ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 39 | የሐድያ ብሔር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 40 | የጌዴኦ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 41 | የየም ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 42 | የአፋር ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 43 | የኦሮሚያ ነጻነት ብሔራዊ ፓርቲ | | |
| 44 | የኦሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት | | |
| 45 | የሲዳማ አርነት ንቅናቄ | | |
| 46 | የዎላይታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር | | |
| 47 | የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 48 | ዱቤና ደገኒ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 49 | የዲል ወቢ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 50 | የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር | | |
| 51 | የሲዳማ ሀዲቾ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 52 | የቤንች ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 53 | የሸኮና አካባቢው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 54 | ዓረና ትግራይ ለዲሞክራሲ ለሉዓላዊነት | | |
| 55 | የአርጎባ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 56 | የሐረሪ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 57 | የጋምቤላ ሕዝቦች አንድነት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 58 | የአርጐባ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 59 | የቤንሻንጉልና ጉሙዝ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 60 | የአገው ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 61 | የቤንሻንጉል ሕዝብ ነፃነት ንቅናቄ ለሠላምና ለዴሞክራሲ ድርጅት | | |
| 62 | የስልጤ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 63 | የደቡብ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኮንግረስ | | |
| 64 | የጋምቤላ ህዝቦች ነፃነት ንቅናቄ | | |
| 65 | የቅማንት ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 66 | ኢትዮጵያዊያን ሀገር አቀፍ ንቅናቄ | | |
| 67 | የኦሮሞ ነፃነት ንቅናቄ | | |
| 68 | የኦሮሞ ብሔራዊ ፓርቲ | | |
| 69 | ነፃነት ለአንድነትና ለፍትሕ ፓርቲ | | |
| 70 | የአፋር ሕዝብ ፓርቲ | | |
| 71 | የጋምቤላ ሕዝቦች ፍትህ ለሰላምና ልማት ዲሞክራቲክ ንቅናቄ | | |
| 72 | የአፋር ሕዝብ ነፃነት ፓርቲ | | |
| 73 | ነፀብራቀ አማራ ድርጅት | | |
| 74 | የአፋር ሕዝቦች ፍትሐዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 75 | የአገው ብሔራዊ ሸንጎ | | |
| 76 | የአፋር ነፃ አውጭ ግንባር ፓርቲ | | |
| 77 | የቁጫ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 78 | ሞቻ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 79 | የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ሕዝብ ህብረት | | |
| 80 | የኦሮሞ ነፃነት ግንባር | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 81 | አርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ | | |
| 82 | ዲሞክራቲክ ፓርቲ ሲዳማ | | |
| 83 | የኢትዮጵያ አረንጓዴ ሊብራል ፓርቲ | | |
| 84 | የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ | | |
| 85 | የጋምቤላ ክልላዊ ንቅናቄ | | |
| 86 | የኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ንቅናቄ | | |
| 87 | የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር | | |
| 88 | የአማራ ሕልውና ለኢትዮጵያ አንድነት | | |
| 89 | ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ | | |
| 90 | የኦሮሚያ ነፃነት ዴሞክራሲ ግንባር | | |
| 91 | የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር | | |
| 92 | የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር | | |
| 93 | የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር | | |
| 94 | ሐረሪ ሪቫይቫል ንቅናቄ | | |
| 95 | የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ | | |
| 96 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሽግግር ም/ቤት | | |
| 97 | የኢትዮጵያ ነፃነት ፓርቲ | | |
| 98 | የኢትዮጵያ መድህን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 99 | ነፃነትና እኩልነት ፓርቲ | | |
| 100 | የኢትዮጵያ ኅብረሕዝብ ብሔራዊ ንቅናቄ | | |
| 101 | የትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 102 | ቱሳ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 103 | ደቡብ አረንጓዴ ኮከብ ኅብረት | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 104 | የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ኅብረት | | |
| 105 | የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት ፓርቲ | | |
| 106 | ነፃነትና ሰላም ለኢትዮጵያ ኅብረት ፓርቲ | | |
| 107 | ብሩህ ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |